## ክፍል ሁለት
## በገጠር መሬት የመጠቀም መብት ስለማረጋገጥ

### ፭. የገጠር መሬት ስለማግኘትና ስለመጠቀም

፩/ በመሬት አስተዳደር ሕግ መሠረት:-

ሀ/ በግብርና ሥራ ለሚተዳደሩ አርሶ አደር ከፊል አርብቶ አደር እና አርብቶ አደሮች የገጠር መሬት በነፃ እንዲያገኙ ይደረጋል፣

ለ/ ዕድሜው ከ፲፰ ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነና በግብርና ሙያ ሊተዳደር የሚፈልግ ማንኛውም የሀገሪቱ ዜጋ በገጠር መሬት የመጠቀም መብቱ የተረጋገጠ ሆኖ እናትና አባታቸውን በሞት ወይም በሌላ ሁኔታ ያጡ ልጆች ፲፰ ዓመት እስኪሞላቸው ድረስ በሀጋዊ ሞግዚታቸው አማካኝነት በገጠር መሬት የመጠቀም መብት አላቸው፣

ሐ/ በግብርና ሥራ መሰማራት የሚፈልጉ ሴቶች የገጠር መሬት የማግኘትና የመጠቀም መብት አላቸው፣

፪/ ማንኛውም በገጠር መሬት የመጠቀም መብት ያለው አርሶ አደር ከፊል አርብቶ አደር እና አርብቶ አደር ቤተሰብ አባል ከቤተሰቡ በስጦታ ወይም በውርስ ወይም አግባብ ካለው ባለሥልጣን የገጠር መሬት በይዞታ ሊያገኝ ይችላል፣

፫/ መንግሥት በመሬት ባለቤትነቱ የወል/የጋራ የገጠር መሬት ይዞታዎችን እንደአስፈላጊነቱ ወደ ግል ይዞታነት እንዲቀየሩ ሊያደርግ ይችላል፣

፬/ ለአርሶ አደሮች ለከፊል አርብቶ አደሮችና ለአርብቶ አደሮች ቅድሚያ በመስጠት፣

ሀ/ በግብርና ልማት ለሚሰማሩ ባለሀብቶች በፌዴራልና በክልል ደረጃ በወጡት የኢንቨስትመንት ፖሊሲዎችና ሕጎች መሠረት በገጠር መሬት የመጠቀም መብት ይኖራቸዋል፣

ለ/ መንግሥታዊና መንግሥስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተቋማት ከልማት ዓላማቸው ጋር እየታየ በገጠር መሬት የመጠቀም መብት ይኖራቸዋል፣

## SECTION TWO
## THE RIGHT TO HOLD AND USE RURAL LAND

### 5. Acquisition and Use of Rural Land

1/ In accordance with land administration law:

a) Peasant farmers/pastoralists engaged in agriculture for a living shall be given rural land free of charge:

b) Any citizen of the country who is 18 years of age or above and wants to engage in agriculture for a living shall have the right to use rural land; children who lost their mothers and fathers due to death or other situation shall have the right to use rural land through legal guardians until they attain 18 years of age:

c) Women who want to engage in agriculture shall have the right to get and use rural land.

2/ Any person who is member of a peasant farmer, Semi pastoralist and pastoralist family having the right to use rural land may get rural land from his family by donation, inheritance or from the competent authority,

3/ Government being the owner of rural land, communal rural land holdings can be changed to private holdings as may be necessary;

4/ subject to giving priority to peasant farmers/semi pastoralists and pastoralist:

a) Private investors that engage in agricultural development activities shall have the right to use rural land in accordance with the investment policies and laws at federal and regional levels;

b) Governmental and non-governmental organizations and social and economic institutions shall have the right to use rural land in line with their development objectives.

**፮. የገጠር መሬትን ስለመለካት፣ ስለመመዝገብና ስለይዞታ ማረጋገጫ ደብተር**

፩/ በግል፣ በወል፣ በመንግሥትና መንግሥታዊ ባል ሆኑ ድርጅቶች ይዞታዎች ያሉ የገጠር መሬቶች እንደሁኔታው ባህላዊና ዘመናዊ የቅየሳ መሣሪያ ዎችን በመጠቀም የመሬት ስፋታቸውን በመለካት እንዲሁም የመሬት አጠቃቀማቸውና የለምነት ደረጃቸው በክልልና በየደረጃው በተቋቋሙ የመረጃ ማዕከላት እንዲመዘገቡ ይደረጋል፣

፪/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) የተዘረዘሩት የገጠር መሬት ይዞታዎች አግባብ ባለው ባለሥልጣን ተለክተው የይዞታ ድንበራቸውን የሚሳይ ካርታ ይዘጋጅላቸዋል፣

፫/ ማንኛውም የገጠር መሬት ባለይዞታ አግባብ ባለው ባለሥልጣን የሚዘጋጅና የመሬቱን ይዞታ ስፋት፣ አጠቃቀምና ሽፋን፣ የለምነት ደረጃና አዋሳኞቹን እንዲሁም ኃላፊነትና ግዴታን የያዘ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር እንዲኖረው ይደረጋል፣

፬/ መሬቱ የባልና የሚስት የጋራ ከሆነ ወይም በሌሎች በጋራ የተያዘ ከሆነ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተሩ በሁሉም የጋራ ባለይዞታዎች ስም መዘጋጀት አለበት፣

፭/ የገጠር መሬት በማን ይዞታ ሥር እንደሚገኝ፣ ከማን መሬት ጋር እንደሚዋሰን፣ ደረጃው ምን ዓይነት እንደሆነ፣ ለምን አገልግሎት እንደሚውልና ባለይዞታው ምን መብትና ግዴታዎች እን ዳሉበት የሚገልጽ መረጃ ተመዝግቦ አግባብ ባለው ባለሥልጣን እንዲያዝ ይደረጋል፣

፮/ በሊዝ ወይም በኪራይ የተያዘ የገጠር መሬት አግባብ ባለው አካል መመዝገብ አለበት።

**፯. በገጠር መሬት የመጠቀም መብት ፀንቶ ስለሚቆይበት ጊዜ**

፩/ የአርሶ አደሮች ከፊል አርብቶ አደሮች እና አርብቶ አደርች በገጠር መሬት የመጠቀም መብት የጊዜ ገደብ የለውም፣

፪/ የሌሎች ባለይዞታዎች በገጠር መሬት የመጠቀም መብት ፀንቶ የሚቆይበት የጊዜ ገደብ በክልሎች የገጠር መሬት አስተዳደር ሕግ መሠረት ይወሰናል፣

**6. Rural land Measurement, Registration and Holding Certificate**

1/ The sizes of rural lands under the holdings of private persons, communities, governmental and non-governmental organizations shall be measured as appropriate using cultural and modern measurement equipments; their land use and level of fertility shall be registered as well in the data base center by the competent authorities established at all levels.

2/ Rural land holdings described under Sub-Article 1 of this Article shall be measured by the competent authority and shall be given cadastral maps showing their boundaries

3/ Any holder of rural land shall be given holding certificate to be prepared by the competent authority and that indicates size of the land, land use type and cover, level of fertility and boarders, as well as the obligation and right of the holder.

4/ Where land is jointly held by husband and wife or by other persons, the holding certificate shall be prepared in the name of all the joint holders.

5/ The information that describes the holder of rural land, the holders of the bordering lands, the types of use, and the rights and obligation of the holder thereof shall be registered in the database and kept by the competent authority.

6/ Any rural land that is held through lease or rental shall be registered by the competent authority.

**7. Duration of Rural Land Use Right**

1/ The Rural land use right of peasant farmers, semi-pastoralists and pastoralists shall have no time limit.

2/ The duration of rural land use right of other holders shall be determined by the rural land administration laws of regions.

## ፱. ስለገጠር መሬት ሽግሽግ

፩/ የመሬቶች ባለይዞታዎቹ በሕይወት የሌሉና ወራሽ የሌላቸው ከሆነ ወይም ባለይዞታዎቹ በሰፈራ ወይም በፍላጐታቸው በክልሎች የገጠር መሬት አስተዳደር ሕግ ከተወሰነው ጊዜ በላይ ከአካባቢው ለቀው የቆዩ ከሆነ በአካባቢው ለሚኖሩት መሬት አልባ ለሆኑ ወይም መሬት ላነሳቸው አርሶ አደሮች፣ ከፊል አርብቶ አደሮች እና አርብቶ አደሮች በሽግሽግ እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡

፪/ የመስኖ መሬትን በአግባቡና በፍትሃዊነት ለመጠቀም በመስኖ መሬት ላይ ሽግሽግ ሊካሄድ ይችላል፣

፫/ በአርሶ አደሮች ከፊል አርብቶ አደሮች እና አርብቶ አደሮች ፍላጎትና ውሳኔ የገጠር መሬት ሽግሽግ ማካሄድ አማራጭ የሌለው ሆኖ ሲገኝ የመሬት ሽግሽጉ ከአነስተኛ የይዞታ መጠን በታች በማይሆንና የተፈጥሮ ሀብት መመናመንን በማያስከትል መልኩ ተግባራዊ መሆን አለበት፣

፬/ የገጠር መሬት ይዞታቸውን ለመስኖ አውታር ግንባታ ሲባል ለሚያጡ አርሶ አደሮች ከፊል አርብቶ አደሮች እና አርብቶ አደሮች በአካባቢው ከሚዘረጋው የመስኖ ልማት ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የመሬት ሽግሽግ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

## ፲. የገጠር መሬት ተጠቃሚዎች ግዴታዎች

፩/ የገጠር መሬት ባለይዞታው መሬቱን በአግባቡ የመጠቀምና የመንከባከብ ግዴታ አለበት፡፡ በመሬቱ ላይ ጉዳት ከደረሰ የመሬት መጠቀም መብቱን ሊያጣ ይችላል፡፡ ዝርዝሩም በክልል የገጠር መሬት አስተዳደር ሕግ መሠረት ይሆናል፣

፪/ የመስኖ ቦዮችና ሌሎች የመሠረተ ልማት አውታሮች በሚዘረጉበት ወቅት በባለይዞታው መሬት ላይ የሚያልፉ ከሆነ ይህንኑ የመቀበል ግዴታ አለበት፣

፫/ ባለይዞታው አግባብ ባለው ባለሥልጣን የገጠር መሬቱ እንዲለካ ወይም የቅየሳ ሥራ እንዲካሄድ ሲጠየቅ የመተባበር ግዴታ አለበት፣

፬/ ማንኛውም የገጠር መሬት ባለይዞታ በመሬቱ የመጠቀም መብቱን በፈቃዱ ሲተው አግባብ ላለው ባለሥልጣን የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

## 9. Distribution of Rural Land

1/ In accordance with land administration laws of the regions farmlands whose holders are deceased and have no heirs or are gone for settlement or left the locality on own wish and stayed over a given period of time shall be distributed to peasant farmers, semi pastoralist and pastoralist who have no land and who have land shortage.

2/ Distribution may be undertaken on irrigable land in order to use irrigable land properly and equitably.

3/ Upon the wish and resolution of peasants farmers, semi pastoralists and pastoralists where land distribution becomes the only alternative, it shall be undertaken in such a way that it shall not be less then the minimum size of holding and in a manner that shall not result in fragmentation of land and degradation of natural resources.

4/ Where peasant farmers, semi pastoralist and pastoralists are evicted from their holdings for purpose of constructing irrigation structure, land distribution shall be undertaken to make them get equitable benefit from the irrigation development to be established.

## 10. Obligations of Rural Land Users

1/ A holder of rural land shall be obliged to use and protect his land. When the land gets damaged, the user of the land shall lose his use right. Particulars shall be given in the land administration laws of the regions.

2/ Where irrigation canals are constructed, the holder shall have the obligation to allow the construction of irrigation lines and other infrastructures if they cross his land holding.

3/ The holder of rural land shall have the obligation to cooperate when requested by the competent authority to measure and survey his land.

4/ Any rural landholder shall have the obligation to notify the competent authority when he abandons at will his land use right.

## ፲፩. የገጠር መሬት አነስተኛ ወለልን ስለመወሰንና ኩታ ገጠም ይዞታን ስለማበረታታት

፩/ ቀደም ሲል የነበረው የአንድ ቤተሰብ ይዞታ ወይም ማሳ ስፋት እንዳለ ሆኖ፣ ወደፊት የሚሰጠው የማሳ ስፋት ከአነስተኛው የይዞታ መጠን በታች መሆን የለበትም፣

፪/ የገጠር መሬት በውርስ በሚተላለፍበት ወቅት የሚተላለፈው የመሬት ይዞታ መጠን ከአነስተኛው የይዞታ መጠን በታች መሆን የለበትም፣

፫/ አነስተኛ ማሳዎች ለልማት አመቺ እንዲሆኑ በአርሶ አደሩ ሙሉ ፍቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የይዞታ ልውውጥ እንዲያደርጉ ይበረታታሉ፣

፬/ የይዞታ ልውውጥ ለማድረግ ፈቃደኛ የሆኑ ገበሬዎች ለመለዋወጥ ያሰቡትን የማሳ ስፋትና የለምነት ደረጃ በቀበሌው አስተዳደር ክልል ውስጥ የሚኖሩ ሌሎች ገበሬዎች እንዲያውቁት ለማድረግ መረጃዎቹ በቀበሌው አስተዳደር አማካይነት እንዲሰራጩ ይደረጋል፣

፭/ በሕብረተሰቡ ጥያቄና ተሳትፎ የሚከናወን የሠፈራና የመንደር ምሥረታ ፕሮግራም የመሬት ኩታገጠምነትን ዓላማ ያደረገ እንዲሆን ይደረጋል።

## ፲፪. የክርክሮች አወሳሰን

የገጠር መሬት ይዞታ መብትን በተመለከተ ክርክር ሲነሳ ጉዳዩ በሚመለከታቸው ተከራካሪዎች በውይይትና ስምምነት እንዲፈታ ጥረት ይደረጋል። በስምምነት ሊፈታ ካልቻለ በተከራካሪ ወገኖች በተመረጠ ሽምግልና ወይንም በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር ሕግ በተደነገገው መሠረት ይወሰናል።

## ክፍል ሦስት
## በገጠር መሬት በአጠቃቀም ረገድ ስለተጣሉ ገደቦች

## ፲፫. የገጠር መሬት አጠቃቀም ዕቅድ ስለማውጣትና ስለተዳፋት፣ በረባርና ረግረጋማ መሬቶች አጠቃቀም

፩/ የአፈር ዓይነትን፣ የመሬት አቀማመጥን፣ የተዳፋትነት መጠንን፣ የአየር ፀባይን፣ የዕፅዋት ሽፋንን እና ሶሺዮ-ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን ባካተተ መልኩ ተፋሰስን መሠረት ያደረገ የመሬት አጠቃቀም መሪ ዕቅድ አግባብ ባለው ባለሥልጣን ወጥቶ ተግባራዊ ይሆናል፣

## 11. Determining Minimum Rural Land Holding Size and Encouraging Land Consolidation

1/ Without prejudice to the former holding or farm plot size of a family, the farm plot to be given in the future shall not be less than the minimum size holding.

2/ Where rural land is transferred by succession, it shall be made in such a way that the size of the land to be transferred is not less than the minimum size holding.

3/ In order to make small farm plots convenient for development, farmers are encouraged to voluntarily exchange farmlands.

4/ The information of the size and level of fertility of the farm plots which farmers intend to exchange holding shall be distributed through kebele administration to let other farmers residing in the kebele know about it.

5/ A settlement and villagization program to be undertaken at the request and participation of the community shall be undertaken taking into account the objective of land consolidation.

## 12. Dispute Resolutions

Where dispute arises over rural land holding right, effort shall be made to resolve the dispute through discussion and agreement of the concerned parties. Where the dispute could not be resolved through agreement, it shall be decided by an arbitral body to be elected by the parties or be decided in accordance with the rural land administration laws of the region.

## PART THREE
## RURAL LAND USE RESTRICTIONS

## 13. Land Use Planning and Proper Use of Sloppy, Gully and Wetlands

1/ A guiding land use master plan, which takes in to account soil type, landform, weather condition, plant cover and socio-economic conditions and which is based on a water shed approach, shall be developed by the competent authority and implemented.